# ዲሽ አተካከል ለፍፁም ጀማሪዎችና ለተካኑ የዲሽ ቴክኒሺያኖች

## በሙለር አይቲ ሶሱሽንስ የተዘጋጀ




---

ሰላም ጤና ይስጥልኝ የፔጃችን ተከታዮች እንደምን አላችሁ ኑሮ እንዴት ይዞአችኋል:: ሁሉ ሰላም ነው? ጥቂት ብንጠፋፋም ግን የመጣነው መጥፋታችንን በፍፁም ሙሉ በሙሉ የሚክስ አዲስና እርስዎን እጅግ በጣም የሚጠቅም ስለ ሳተላይት ዲሽ አተካከልና መወሰድ ያለባቸው ጥንቃቄዎች ዙሪያ ዘርዘር ያለ መረጃ ይዘን ነው፡፡ ይህ ዛሬ ይዘን የመጣነው መረጃ በተለይ ለፍፁም ጀማሪዎች ከራሳቸውና ከዲሽ ሰሪ አጋሮቻቸው ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች ከሚወስዷቸው ትምህርት ተጨማሪ የተወሰነ ግን መሠረታዊ የሆነ ጠቀም ያለ መረጃ ነው ፡፡ ብዙ ሰላምታና ማብራሪያ ሳነበዛ ወደሚያጓጓው ትምህርታዊ ፅሁፋችን እናምራ፡፡

ዲሽ ለመጀመሪያ ጊዜ ለመትከልና ለመግጠም የተሰማሩ የዲሽ ባለቤት ግለሰቦች ፡ ጀማሪ ወይም ልምድ ያላቸው ቴክኒሺያኖች መያዝ የሚገባቸው የሳተላይት ዲሽ መግጠሚያ መሳሪያዎችና አጠቃቀማቸው፡-

- ማንኛውም የሳተላይት ዲሽ ቴክኒሺያን በቅድሚያ የሚገጥመውን የሳተላይት ዲሽ አይነትና አቅጣጫ በአትኩሮትና በበቂ ሁኔታ ከምንም በላይ መገንዘብ ይኖርበታል፡፡

- በአብዛኛው በሃገራችን የሚገጠሙና ስርጭታቸው በሰፊ ከሚገኙ የሳተላይት ዲሽ ቻናሎች

ለመጥቀስ ያህል በየቤታችን የሚገኘውና እጅግ ብዙ ተጠቃሚዎች ያሉት የናይልሳትና ከ 5 እና 6 አመታት በፊት ሁሉም የሀገራችን ብሎም ተወዳጅ የውጭ ቻናሎች ይገኙበት የነበረው አሁን በአረቡ አለም ዘንድ ብቻ በስፋት በጥቅም ላይ የሚውለው የአረብሳት ቻናል እና ነፃ የኪስ ቻናሎች ማለትም ቨርዛሽ ቲቪ፣ ቶሎዶ ቲቪ እና ሌሎችን የእንግሊዝና ስፔን ላሊጋ ብሎም፣ የቻምፒዮንስ ሊግ ጨዋታዎችን የሚያስተላልፉ ቻናሎች የሚገኙባቸው የያህሳት ቻናል ዲኤስቲቪ እና የ ፓወር ቪዩ ቻናሎች የሚገኙ ሲኖን እንደ አንድ የሳተላይት ዲሽ ጀማሪም ሆነ የተካነ ቴክኒሺያን ማወቅ ከሚገቡን ነገሮች መካከል የእያንዳንዱን ቻናል አቅጣጫና አቀማመጥ ነው፡፡ እነዚህን ቻናሎች በአግባቡ ለመትከል እንዲረዳን የአቅጣጫ ጠቋሚ ማለትም ኮምፓስ መጠቀም በብዛት የሳተላይት ዲሾችን ለመግጠም ጥቅሙ እጅግ ከፍ ባለ ደረጃ የሚረዳን ሲሆን አጠቃቀሙን በቀጣይ ፅሁፋችን ከፍተኛ አትኩሮት ወደምንሰጥበት መሰረታዊ ፅንሠ ሃሳቦች ጋር ይዘን በሰፊው እንመለስባቸዋለን፡፡

- ማንኛውም የሳተላይት ዲሽ ለመትከል የተዘጋጀ ጀማሪም ሆና የተካነ ባለሙያ መያዝ ያለባቸው እጅግ መሰረታዊና የምንጊዜም አጋዥ መሳሪያዎች መካከል የሚከተሉትን መዘርዘር ይቻላል፡፡

1. በተለምዶ አስር ቁጥር ብለን የመንጠራው የብሎን መፍቻ ለባለ 60 ሴንቲሜትር ሳህንና (ለ 90 ሲንቲሜትርና ከዛ ክፍ ለሚሉ የዲሽ ሳህኖች፣ 10 ቁጥርን ጨምሮ እንደአስፈላጊነቱ 10፣11፣12፣ እና ከዚያ በላይ ያሉት መፍቻዎች በተናጠል ወይም (በህብረት) ማለትም በአንድ የብረት ዘንግ ሶስቱንም በስሩ የያዘ መፍቻ ወይም ከአነስተኝ እስከ ከፍተኛ የብሎን አናት ቁጥሮችን በማጥበቅና በማላላት የምንጠቀምበት በተለምዶ ካበ እንግሊዝ (Wrench) ብለን የምንጠራውን ባለ አንድ ወጥ በጣት በማሽከርከር እንደ ብሎኑ አናት መጠን የሚጠብና የሚሰፋ መፍቻ በቅርብ ከሚገኝ የህንጻ መሳሪያ መደብር መግዛትና ሁሌም ዲሽ ለመትከልም ሆነ ለማስተካለል በምንቀሳቀስበት ጊዜና ቦታ መያዝ፡፡
2. የሚቻልና አቅማችን ከፈቀደ (በተለይ ዲሽ መትከልን እንደ ዘላቂ ሙያ ለያዙ) ሙሉ በሙሉ ዲጂታል የሆነ የሳተላይት ማሰሻ ወይም Finder በመግዛት ለአስፈላጊው ስራ መዘጋጀት፡፡ አቅም የማይፈቅድ ከሆነም ቆየት ያለውን ነገር ግን ላዩ ላይ ዲጅታል ፋይንደር የሚል ፅሁፍ ያለውንና ከ 0 እስከ 10.5 ዲ.ቢ. የሚለካውን ባለ ሜትሩን የሳተላይት ዲሽ ማሰሻ ከ 400 ብር ባልበለጠ ገንዘብ በአካባቢያችን በሚገኙ የኤሌክትሮኒክስ እቃዎች መሸጫ መደብሮች መግዛትና መያዝ፡፡ ለስራችን ቅልጥፍና የሚረዳን የመጀመሪያው አይነት ዲጅታል ፋይንደር ሲሆን የራሱ የሆነ የባትሪ ሀይል ስላለው መብራት እንኳን ቢጠፋ ጣራ ላይ ባለንበት ስራችንን ለመጨረስ ያስችለናል በተጨማሪም የፋይንደሩ ሰሌዳ ላይ ልክ ሪሲቨሩ ላይ እንደምናየው ሲግናልና ኳሊቲ

ማንበቢያ ስላለውና የምንፈልጋቸውን የቻናል ፍሪኩዌንሲዎች ሞልቶ ስለሚይዝልን ስራችንን እጅግ ፈጣን ያደርግልናል፡፡ እጅግ በጣም የሚያስፈልገን ከሆነ ደግሞ በአንገት የሚንጠለጠል የምናስሰውን ቻናል በፋይንደሩ ስሌዳ ላይ ልክ እንደ ቴሌቪዥን ምስሉን በጥራት የሚያሳይ ድምፁንም በጥራት የሚያሰማ ሲግናልና ኳሊቲ ማንበቢያ ያለው እጅግ ዘመናዊ የሆነ ፋይንደር ገዝተን ስራችንን በጣም በዘመናዊ መልኩ ማካሄድ እንችላለን፡፡

3. ከ ፋደራችን አይነትና አቅም ጋር የሚሄድ ተወርዋሪ ገመድ ከዲሹ ጋር ከሚመጣው RG-6 Coaxial Cable (የዲሽ ገመድ) ወይም ከቴሌቪዥን የውጭ አንቴና ጋር ከሚመጡ በውስጣቸው ቀጭን የኮፐር ወይም መዳብ ዘንግ ከያዙ ገመዶች ቆርጦ ርዝመቱ ከ 60 ሳንቲሜትር ያላነሰ ተወርዋሪ ገመድ (Jump Caple) በሁለቱም በኩል የሴቴ ወይም (Female Connector) የያዘ ገመድ ማዘጋጀት፡፡ የገመዱ ጫፍ አንደኛው ወደ የዲሹ ጭንቅላት (LNB) ላይ የሚታሰር ሲሆን ሌሌኛው ጫፍ ፋይንደሩ ላይ (To LNB) በሚለው አቅጣጫ የሚታሰር ይሆናል፡፡ የፋይንደርን አጠቃቀም ወደ ፊት ሰፋ ያለ ትንታኔ የምንሰጥበት ስለሆነ ለዛሬው እዚህ ላይ እንግታው፡፡

4. ተወርዋሪ ገመድ ወይም ከዲሹ ጋር አብሮ የሚመጣውን ገመድ ጫፎች ለመላጥ፣ Female Connector ችን ለማያያዝ፣ ገመዶችን ለማሳጠር ወይም ለመቀጠልና ለማስረዘም እንዲረዳን አንድ ጥሩ የሆነ ፒንሳ ያስፈልገናል፡፡ በአቅራቢያችን ማግኘት የምንችል ከሆነ ደግሞ ኬብል ስትሪፐር ወይም ኬብል ከተር መግዛት ስራችንን ቀልጣፋ ያደርግልናል፡፡

5. የዲሹን LNB ማቀፊያ ለማጥበቅና ለማላላት ብሎም LNB ለመቀየርና አዳፕተሮችን ለመፈታታትና ለማጥበቅ ሊረዳን የሚችል በሁለቱም በኩል ሲቀያያር ጠፍጣፋና ባለ መስቀል አናት የሚሰጥ ካቻቢቴ መያዝ ይጠበቅብናል፡፡

6. የዲሹን ሳህን እግር በሁለት አቅጣጫ ረዘም ካሉ ጣውላዎች ጋር መምቻና የዲሹን ገመዶች በየግድግዳው በኬብል ክሊፕ ለማያያዝና ሌሎች ጠንከር ያለ ሀይል የሚጠይቁ ስራዎችን ለማከናወን የሚጠቅመንን አጠርያለ የፕላስቲክ እጀታ ያለው መዶሻ ያስፈልገናል፡፡

ከላይ የጠቀስናቸው መሳሪያዎች እጅግ መሰረታዊና አስፈላጊ ሲሆኑ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ደግሞ አስፈላጊነታቸው በጣም ብዙም ባይሆን እንኳን መያዛችን ግን ጥቅሙ እጅግ ያመዘነ ይሆናል፡፡

- በማንኛውም ሁኔታ ቢሆን ሊጠቀሙን ስለሚችሉ በርከት ያሉ የ Female connector, Audio Video Splittor Conector ንና ከሁለት ያላነሱ Disqe Switch መያዝ፡፡

- እንደየ ፍላጎታችን የምንሞላውን ሳተላይት መሠረት ያደረጉ የተለያዩ ፊሪክዌንሲዎችና፣ ፖላራይዜሽሮች ዝርዝር በጥንቃቄ ለማወቅ ይረዳን ዘንድ እና አዳዲስ መረጃዎችን በማይረሱ መልኩ ለመፃፍና በአስፈላጊ ጊዜ ዋቢ ለማድረግ ለመፃፊያነት የሚረዱን መጠናቸው እንደየ ግል ፍላጎታችን በሚወሰኑ ማስታወሻ ደብተሮች ላይ ማስፈር፡፡ ለዚህም ይረዳን ዘንድ ለአያያዝ አመቺ የሆኑ ማስታወሻ ደብተሮችን በአቅራቢያችን ከሚገኙ የፅህፈት መሳሪያ መደብሮች ገዝቶ መያዝ፡፡

- የስራው ባህሪ ሆኖ ብዙዎች ተገልጋዮችን የምናገኛቸው በተንቀሳቃሽ ሞባይል ስልኮች ከመሆኑ የተነሳ የኔትወርክ ግኑኝነት በማይኖረበት ቦታ የኔትወርክ ግኑኝነትን አስሰውና ፈልገው የሚያመጡልንን ዘመኑ ኖርማል ሀንድሴት ብሎ የሚጠራቸውን ግን በባትሪ ቆይታቸውና ከቦታ ቦታ ወድቀውም ሆነ በአስቸጋሪ ሁኔታ ተገኝተው በመነሳት አሁን በገበያ ላይ ከሚገኙ የተንቀሳቃሽ ስማርት ስልኮች የላቀ አቅም እንዳለቸው ያስመሰከሩ ተንቀሳቃሽ ስልኮችን መያዝ፡፡ የስማርት ስልክ መያዝ ወቅቱ ያፈራቸውን መረጃዎች በአቅራቢያችን እንዲኖሩንና ሌሎች ተጨማሪ ነገሮችን ያለ ብዙ ድካም ለማግኘት ስለሚረዱን በጥንቃቄ ከተያዙ የማይከፉ ቢሆንም ከላይ በተጠቀሱት ምክኒያቶች አብዝቶ መጠቀሙ ጉዳቱ የሚያመዝን መስሎ ስለሚታየን በተገልጋዮች ዘንድ የሚገኘውን የሲምካርድ ቁጥር በኖርማል ሀንድሴትዎ፣ ለግላዊ ጉዳይ የሚጠቀሙበትን ሲም ካርድዎ ደግሞ በስማርት ስልክዎ በማድረግ የተለመደ ህይወትዎን ከቢዝነስ ህይወትዎ በተለያዩ ሁለት ሲም ካርዶች አማካኝነት እንዲመሩ እንመክራለን፡፡

- አንድ ባለ አንድ አውትፑት (ገመድ ተቀባይ) LNB እና አንድ ባለ ሁለት አወትፑት LNB ዎች ብንይዝ ለስራ በምንጓጓዝበት ወቅት የተቃጠሉ፣ ጉዳት የደረሰባቸውን፣ የደከመ የምስል ጥራት የሚያወጡ LNB ዎችን ለመለየትና በምትኩ በመግጠም ከአላስፈላጊ ድካምና ወጪ ራሳችንን ማዳን እንችላለን፡፡ ያስታውሱ ሁሌም የተቃጠለ፣የተጎዳ ወይም የደከመ የምስል ጥራት የሚያወጣ LNB በአዲስ በምንተካበት ወቅት ወዲያውኑ በምትኩ ለራሳችን መግዛት እንዳለብን በፍፁም መዘንጋት የለብንም፡፡

- በቤት ኪራይ ምክኒያት ሰዎች ከቦታ ቦታ ሲንቀሳቀሱ ከዚህ ቀደም የነበረው የዲሽ ገመድ ሳህኑን ከምንተክልበት አዲስ ቦታ ራቅ ያለ ሊሆን ስለሚችልና በተለያየ አጋጣሚ ገመዶች የመተጣጠፍና የመቀጥቀጥ አደጋዎች ስለሚደርስባቸው ለመቀጠያና ለመተኪያ የሚሆን ከ20 ሜትር ያላነሰ የዲሽ ገመድ ለአያያዝ አመቺ በሆነ መልኩ መያዝ፡፡ ከገመዱ የሚጠቀሙትን በሜትር አስልተው ከሙያ ዋጋ ክፍያዎ ጋር ማስከፈልዎንና በምትኩም አዲስ ገመድ መግዛትን አይርሱ፡፡

- ነፃ የኳስ ቻናሎችን ወይም ሁለት LNB የሚጠይቁ ስራዎችን በምንሰራበት ወቅት

ለተጨማሪው LNB ትክክለኛ መቀመጫ ቦታ ይሆን ዘንድ በጋራጅ ቤቶች ለዚሁ አገልግሎት የተሰራ ዘንግ (የገበያ ስሙም ዘንግ ነው) መግዛትና መያዝ፡፡

- በተለያዩ ቦታዎች ለማጠናከሪያነት ሊጠቅሙን የሚችሉ የተለያዩ አይነት ሚስማሮችን መያዝ፡፡
- ገመዶች እንዳይጠላለፉና ውበታቸውን ጠብቀው በግድግዳዎች ላይ እንዲሄዱ የሚያስችሉንን ትክክለኛ መጠን ያለቸውን የገመድ ክሊፖች መያዝ፡፡
- የገመዶችን ርዝመት ለመለካትና ከዚያም በላይ ለተጨማሪ የሚለኩ ነገሮች የሚያገለግል ሜትር፡፡
- የሳህኑን አናትና እግር ካሰርንና እንዳይነቃነቅ ካጠባበቅን በኋላ በትንሽ መነካካት ኳሊቲያቸው ሊወርዱና ሊወጡ የሚችሉ ሳህኖች በንፋስ ሀይል በቅርቡ ሙሉ በሙሉ ኳሊቲያቸው ሊወርድ ስለሚችል ይህንን እንዲቋቋምልን የሚያስችለንን ሽቦ ከተመታው የቆርቆሮ ሚስማር ጋር መወጠር፡፡ እንደዚህ አይነት አጋጣሚዎች ሊበዙ ስለሚችሉ የተጠቀለለ ሽቦ መያዝ፡፡
- ከላይ የተጠቀሱትን መሳሪያዎችና አንዳንድ ከቦታ ቦታ ስንንቀሳቀስ የሚያስፈልጉንን የግል ንብረቶቻችን መያዣ የሚሆን የጀርባ ሻንጣ ሊኖረን ይገባል፡፡ ከዚህ የጀርባ ሻንጣ አንድ በአንድ የምናወጣቸውን የተለያዩ መሳሪያዎች ስራችንን ከጨረስን በኋላ መልሰን ማስገባታችንን ሁሌም ቢሆን ማረጋገጥ ይኖርብናል፡፡
- ለማስተካከል ወይም አዲስ ለመትከል እየተዘጋጀንለት ያለናቸው ሪሲቨሮች አጠቃቀማቸውን በራሳችን ፍለጋ ማግኘት ወይም አሰራሩ የተዋሀደው የዲሽ አሰሪ አካል ትብብር መጠየቅ (ብዙ ጊዜ እጅግ ያረጁና አጠቃቀማቸው ግራ የሚያጋባ ሪሲቨሮች ይገጥሙናል በዚህ ጊዜ ማድረግ የሚገባን አንድ ነገር ቢኖር መጀመሪያ ራሳችንን ማረጋጋት ሲሆን ሲቀጥል እንደየ እድሜያቸውና እንደኛ አቅም፣እና እንደየ ፋብሪካ ስሪታቸው የሪሲቨሮቹን አሰራር መረዳት ሲሆን ብዙዎቹ ቆየት ያሉ ሪሲቨሮች በመጠኑ አዳጋችና ለመረዳት ሰፋ ያለ ጊዜን የሚወስድ ሶፍትዌር የተጫነባቸው ናቸው ይሁንና ያለንን መጠነኛ የእንግሊዝኛ አቅም በመጠቀም እኚህን ሶፍትዌሮች በቀላሉ ከ 5 ደቂቃ ባለነሰ መልኩ ከራሳችን ጋር ማዋሀድ እንችላለን፡፡) ይህንንም ድርጊት ማከናወን የአሰራር ፍጥነታችንን እጅግ የሚያዳብረው ይሆናል፡፡
- በተለያዩ ምክኒያት የሚፈጠሩ የምስል ጥራት መጓደል፣ የኳሊቲ ማነስና ሎሎች ተዛማች ችግሮችን በፍጥነት ለመለየት የሚያስችል ከተለያዩ ምንጮች የተገኘ እውቀትና ራስን ሙሉ በሙሉ ከዘመኑ ጋር እኩል ለማድረግ የሚያስችል ተጨባጭ

ክህሎት ለማዳበር ራስን በተለያየ መልኩ ማብቃት፡፡

- የዲሽ ስራ በባህሪው ከቦታ ቦታ መዘዋወርን የሚጠይቅ ስለሆነ ሁሉም ቦታዎች ላይ ደግሞ በሚኒባስ፣ በባጃጅ ወይም በጋሪ መድረስ ስለማይቻል የራሳችን የሆነ ከቦታ ቦታ ለመንቀሳቀሻነት የምንጠቀምበት ሞተር ሳይክል ቢኖረን ጥሩ ነው፡፡ አቅማችን ሞተር ለመግዛት የማይፈቅድ ከሆነ ደግሞ በኤሌክትሪክ የሚሰራ ቻርጅ ከተደረገ በኋላ ብዙ ኪሎሜትሮችን መጓዝ የሚችል ካቴና በተመታ ቁጥር ተጨማሪ ሀይል የሚሰጥ (Scooter) በመባል የሚታወቅ መንቀሳቀሻ በመግዛት መኪናና ባጃጆች ሊገቡባቸው የማይችሉ ጉራንጉሮች ውስጥ ሁሉ ሳይቀር የተቀላጠፈ ስራ መስራት ይቻላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ያሉበት ከተማ ዳገት የመይበዛበት ከሆነ ብስክሌት በመግዛት የፈለጉበት ቦታ ድረስ በመሄድ ስራዎን ማከናወን ይችላሉ፡፡

ማንኛውም የዲሽ ባለሞያ ለስራ በሚንቀሳቀስባቸው ጊዜያት ሊወስዳቸው የሚገቡ ጥንቃቄዎችና የስነምግባር መመሪያዎች

- ከምንም ከማንም በላይ ለራሳችን ህይወት ከፍተኛ የሆነ ጥንቃቄ ማድረግ፡፡ በመሰላል በምንወጣጣበት ወቅት ከሁሉም አስቀድመን የመሰላሉ ማንኛውም አካል ለአደጋ የሚያጋልጥ አለመሆኑን በተደጋጋሚ ማረጋገጥ፡፡ መሰላሉ የሚቆምበት ቦታ የተደላደለ መሆኑን ማረጋገጥ፡፡ በምንወጣበትና በምንወርድበት ጊዜ መሰላሉ ወደ ጎንና ወደ ኋላ እንዳይንሸራተት በሰው ማስያዝ፡፡ የተበላሹ የሚነቃነቁ፣ በርጥበት የተጎዱና በምስጥ የተበሉ መሰላሎች በሚኖሩበት ወቅት ከጎረቤት የተሻለና አስተማማኝ መሰላል እንዲመጣልን የዲሽ አሰሪዎችን መልካም ትብብር መጠየቅ፡፡ አስተማማኝ መሰላሎች በማይገኝበት ወቅት እራስን አደጋ ውስጥ ከማስገባት በፊት ተለዋጭ ቀጠሮ በመስጠት አስተማማኝ መሰላል ሲገኝ ስልክ እንዲደወልልን ማድረግ፡፡ ብዙ የሆነ መውጣትና መውረድ ለአደጋ እንዳያጋልጠን ነገሮችን አስቀድመን መሬት ላይ መጨረስ ለምሳሌ የዲሹን እግር ከጣውላዎች ጋር መምታትና የመሳሰሉት፡፡
- እንደሚታወቀው የአብዛኞቻችን የሀገራችን ቤቶች የተሰሩት ከእንጨትና ከቆርቆሮ በመሆኑና የሚተከሉት የዲሽ ሳህኖችም ምርጥ ኳሊቲ እንዲገባልን ሲባል ጣራ ላይ በመሆናቸው ጣራ ላይ ከወጣን በኋላ አግዳሚ ማገር ላይ የተመቱትን የቆርቆሮ ሚስማሮች እንደ አመላካች በመጠቀም በጥንቃቄ መራመድ ይኖርብናል፡፡ ለሳህኑ እግር መቀመጫ ቦታ ስንመርጥም ሳህኑ እንዳይንቀሳቀስ ለማጠናከር የምንጠቀምበትን ድንጋይ ወይም ብሎኬት ጫና መቋቋም እንዲችል አግዳሚ ማገሩ ላይ መሆን ይኖርበታል፡፡ ሌላው መውሰድ ያለብን ጥንቃቄ የቆርቆሮ ጠርዞችን የተመለከተ ሲሆን በምንም አይነት መልኩ እንዲቆርጡን መፍቀድ የለብንም፡፡ ቆየት ብለው የተሰሩና ያረጁ ጣራዎች በብዛት በዝገት ስለሚጠቁ የእኛን ክብደት የመቋቋም አቅማቸው እጅግ

የተዳከመ ሊሆን ስለሚችል አስፈላጊውን ጥንቃቄ መውሰድ ይገባናል፡፡ በስህተት ማገር ላይ ያልተመታ ቆርቆሮ ላይ በምንረግጥበት ጊዜ የመሰርጎድና ከበድ ያለ የሚንቋቋ ድምፅ ስለሚሰጠን ፈጠን ብለን እግራችንን ማገር ላይ ወደ ተመታው ቆርቆሮ መመለስ ይኖርብናል፡፡ እንደ ድንጋይ፣ብሎኬትና የመሳሰሉትን ከበድ ያሉ ነገሮችን ወደ ጣራ ይዘን በምንወጣበት ወቅት ከፍተኛ ጥንቃቄዎችን ማድረግ ይገባናል፡፡

- ምንም እንኳን የተቻለንን ጥንቃቄ ብናደርግም በተለያየ የስራ አጋጣሚ ሊደርሱብን የሚችሉ ቀለል ያሉ ጉዳቶች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ በመሆኑም አንድ አነስ ያለች የመጀመሪያ ህክምና እርዳታ መስጫ መሳሪያዎችን የያዘች ሳጥን ቢኖረን እጅግ በጣም ጥሩ ነው፡፡ በውስጧም በርከት ያሉ የቁስል ፕላስተሮች፣ ንፁህ ጥጥ፣ ፋሻ፣ የተጠቀለለ ነጭ የቁስል ፕላስተር፣በፕላስቲክ ጠርሙስ የታሸገ አልኮል (በተለምዶ ጂቢ የምንለው) እና ሌሎችንም የያዘች ብትሆን እጅግ በጣም ተመራጭ ነው፡፡ ያስታውሱ ምንጊዜም ቢሆን ለጥንቃቄ ቅድሚያ መስጠት ይኖርብናል፡፡ ድንገት እንኳን በዛገ ቆርቆሮ ወይም ሚስማር የመቆረጥ ወይም የመወጋት አደጋ ቢገጥመን የመንጋጋ ቆልፍ በሽታ ተጠቂ እንዳንሆን በፍጥነት በአልኮል በተነከረ ንፁህ ጥጥ የተቆረጠውን የሰውነታችን ክፍል በማከም በቁስል ፕላስተር አሽገን በአቅራቢያችን ወደሚገኝ የህክምና ተቋም መሄድ ይኖርብናል፡፡

- በክረምት ወራት በዝናብ ምክኒያት በሚኖር ርጥበት መሰላሎችና ጣራ ላይ አዳልጦን የመውደቅ አደጋ እንዳይደርስብን ርጥበቱ ሙሉ በሙሉ ተወግዶ እንኪደርቅ ድረስ መጠበቅ ይኖርብናል፡፡ በበጋና እጅግ ፀሀያማ በሆነ ወቅት በፀሀይ ብርሃን ምክኒያት የቆርቆሮ ጣራዎች በተለይም ከ ረፋዱ 5:30 ሰአት ጀምሮ እስከ ቀትሩ 9:30 እጅግ ከፍተኛ ሙቀትና ግለት ስለሚፈጥሩ ስራችንን በአግባቡና በተዝናኖት እንዳናከናውን ከፍተኛ የሆነ መሰናከል ሊሆኑብን እንደሚችል ግልፅ ነው በመሆኑም በተቻለ መጠን ከተጠቀሱት ሰአታት ውጭ ባሉት ጊዜያት ስራችንን በአግባቡና በተረጋጋ መንፈስ ማድረግ ይሮርብናል፡፡ በከፍተኛ ሙቀት ላይ ጣራ ላይ ወጥቶ ለረጅም ጊዜ መቆየት የአይን ብዥታን፣ያልታሰበ በአፍንጫ  ውስጥ ደም መውረድ (ነስር) ፣ ራስ ማዞርና የእይታ በከፊል መጋረድ፣ ከባድ ራስ ምታትና ማናጃይትስ ወይም ማጅራት ገትር እንደሚያስከትል ጥናቶች ይጠቁማሉ፡፡ ወደ አለባበሳችን ደግሞ ስንመጣ እግራችንን እንደፈለግን የሚያንቀሳቅሱንን ሱሪዎችንና (እንደ ቱታ ያሉ) በቀለማቸው ሙቀትን የማይስቡ (ከጥቁር ከነጭ ውጭ የሆኑ) ነፀብራቅን የማይፈጥሩ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ ጫማዎቻችን የታችኛው ሶላቸው በደንብ መሬት መቆንጠጥ የሚችልና ሙቀት አዝልቀው የማያስገቡ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ ኮፍያዎችን የፀሀይ ሙቀት ሃያል በሚሆኑባቸው ጊዜያቶች ማድረግ ጥቅሙ የጎላ ሲሆን ነገር ግን ኮፍያዎችን ለረጅም ጊዜ ማድረግ ራሰ በራነትን ሊያስከትል ስለሚችል አደራረጋችን ላይ ገደብ ልናበጅለት

ይገባል፡፡

ማንኛውም የዲሽ ባለሞያ ሊኖረው የሚገቡ ስነ-ምግባራት

- ሁሉንም የህብረሰብ ክፍል ፍፁም ትህትና በተሞላበትና በቀና መንገድና በእኩል አይነት መንገድ ማስተናገድ
- በስልክም ሆነ በአካል ከማንኛውም የህብረሰብ ክፍል የሚመጡ ቅሬታዎችን በቅን አእምሮ ተቀብሎ በአግባቡ ትህትና በተሞላበት መልኩ ማስተናገድ
- ለሰራበት ስራ ተገቢውን የሆነ ክፍያ መጠየቅና በተቻለ መጠን በኢኮኖሚያቸው ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ለሚገኙ የማህበረሰብ ክፍሎች አስተያየት በማድረግ መጠነኛ ክፍያ ማስከፈል
- አገልግሎት በሚሰጥበት ሰዓት የመጨረሻ አቅሙን ተጠቅሞ ጥራት ያለው የማያዳግም ስራ በመስራት ደንበኞቹን ለማርካት የላሰለሰ ጥረት ማድረግ፡፡ ከአቅም በላይ ለሚሆኑ ችግሮች ቀደም ያለ ጥልቅ እውቀትና ግንዛቤ ላላቸው የስራ አጋሮች ግልፅ የሆነ ጥያቄ ማድረግ፡፡
- አገልግሎት እንዲሰጥ ጥሪ በሚደረግለት ሰዓት ቦታው ለመድረስ የሚወስድበትን ጊዜ ገምቶ ማሳወቅና በሰዓቱ መገኘት፡፡ በስራ መደራረብ ወይም በተለያያ ግላዊ ምክኒያቶች ደንበኞችን ማስተናገድ የማይችልበት ሁኔታ ሲከሰት ለሌሎች በቅርብ ለሚገኙ የስራ አጋሮቹ ማስተላለፍ ወይም እንደማይመቸው መግለፅ፡፡
- በገበያው ላይ የሚገኙትን ትክክለኛ የዲሽ እቃ ዋጋዎች ለህብረተሰቡ ግልፅ በማድረግ ግልፀኝነትን ማስፈን
- በራስ ላይ አደጋ ሊጥሉ የሚችሉ ወይም ተመሳሳይ ይዘት ያለቸውን ስራዎችን ለራስ ክብርና ለሀገሪቱ ህልውና ሲባል ባለመስራት የዜግነት ግዴታን መወጣት
- ባለው እውቀት ያለመመካትና ከሌሎች ዲሽ ቴክኒሻኖች ጋር ያለ ምንም ክፍያ የሚያውቁትን በግልፅ ማካፈልና በተለያዩ የመወያያ መድረኮች የሚገበዩትን እውቀት ለአጋር ባለሞያዎች በስፋት ማዳረስ፡፡
- እና ሌሌች መልካም ስነምግባርን የሚያመላክቱ ስራዎችንና ባህሪያትን ማዳበር

ውድ አንባቢያን ከፅሁፉ መጠነኛ ትምህርት እንዳገኛችሁበትና እንደወደዳችሁት ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ በቀጣይ ከዚህ ፅሁፍ ጋር በተያያዘ ተከታታይ ፅሁፎችን በጥሩ ትንታኔ አጅበን ይዘን እንድንመጣ ያግዘን ዘንድ የፌስቡክ ገፃችንን ላይክ በማድረግ ኮሜንት በመፃፍና ኮፒ

ፔስት ከማድረግ ታቅበው ይህንን ፅሁፍ ሼር በማድረግ ጥቂት አእምሮአዊ እርካታ እንድናገኝ እንዲረዱን በትህትና እንጠይቃለን፡፡ በቀጣይ አስተማሪ ፅሁፋችን እንስክንገናኝ ድረስ ሰላሙን ሁሉ ያብዛላችሁ እላላሁ፡፡ ሙለር ነኝ፡፡

የፌስቡክ ገፃችንን ላይክ ሼርና ኮሜንት በማድረግ እርስበርስ እንማማር፡፡

https://www.facebook.com/mulerhitechsolutions

ለበለጠ መረጃ ፣ለአዳዲስ ፍሪኩዌንሲዎች፣ ለትኩስ ቴክኖሎጂ ነክ መረጃዎች እና ለሞያ አዘል ፅሁፎች የቴሌግራም ቻናላችንን አሁኑኑ ይቀላቀሉ በርግጠኝነት ብዙ ነገር ይማሩበታል፡፡ http://www.me/muleritsolutions

Like! Like! Like! Like! Like! Like! Like! Comment and Share!

